# ውበት

አብርሃም በየነ

ፍክክ ፍንድቅ ያሉ
ዕምቡጥ አበባዎች
ውበት የተኳሉ
ከወላድ ማህፀን ይፈለቀቃሉ፤
ግና ምን ያደርጋል
የሰው ስነ-ፍጥረት አበባ ሆነና
ውበቱ ጠውልጎ ይረግፋል በርጅና።

# ዕርጅና

ልብ ሲገሰግስ ጉልበት እየራደ
የስንቱን ህሊና እርጅና አዋረደ፤
ከድህነት ሌላ የሰው ክብር ገዳይ
እንደ ዕርጅና የለም በዚህች ምድር ላይ።

# አዲሱ ጉልተኛ

ከጠለምት ወልቃይት፤ ከጠገዴ አጅሬ
የተወለደውን ጢሰኛ ጎንደሬ
የራያን  የቆቦን…. የወሎን ገበሬ
አዲሱ ጉልተኛ “ባላባቱ” ትግሬ
ጭቃ ሹም ምስለኔ አስጠማኝ በርስቱ
ዕርቦ ተሰፋሪ ሆኗል በመሬቱ።

ጥር 2004